# ሳምንታዊ የቢዝነስ መረጃዎች

**በኮሙኒኬሽንና ህዝብ ግንኙነት መምሪያ የሚዘጋጅ**

*(ከመስከረም 1- 07/2016 ዓ.ም)*
(September 10- 17/2024)

**1.ጂቡቲ የታጁራ ወደብን በጋራ ለማስተዳደር እንጂ ለኢትዮጵያ አሳልፋ እንደማትሰጥ ገለጸች የጂቡቲ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር**

**September 15, 2024**

ኢትዮጵያ ታጁራ ወደብን በጋራ እያስተዳደረች እንድትጠቀምበት እንጂ ጠቅልላ እንድትወስደው ወይም እንድትገዛው የጂቡቲ መንግሥት ሐሳብ አለማቅረቡን የአገሪቱ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ገለጹ።

የጂቡቲ መንግሥት በኢትዮጵያና በሶማሊያ መካከል የተፈጠረውን ውጥረት ለማርገብ በማሰብ፣ ኢትዮጵያ የታጁራ ወደብን መቶ በመቶ በማስተዳደር እንድትጠቀምበት ምክረ ሐሳብ ማቅረቡን ለቢቢሲ የተናገሩት የጂቡቲ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሞሐመድ አሊ ዩሱፍ፣ ይህ ንግግራቸው በጂቡቲ ማኅበረሰብ ዘንድ ብዥታ መፍጠሩን ተከትሎ፣ ባለፈው ሰኞ ቀን በአገሪቱ ቴሌቪዥን ተጨማሪ ማብራሪያ ሰጥተውበታል።

https://www.ethiopianreporter.com/133390/

**2.መንግሥት ፖታሽ ለማምረት ፈቃድ የወሰዱ ኩባንያዎች ሥራ ካልጀመሩ ዕርምጃ እንደሚወስድ አስጠነቀቀ**

*ሪፖርተር፡* **September 15, 2024**

መንግሥት ፖታሽ ለማምረት ፈቃድ የወሰዱ ኩባንያዎች ሥራ ካልጀመሩ ዕርምጃ እንደሚወስድ አስጠነቀቀ፡፡

የግብርና ማዳበሪያ በአገር ውስጥ ለማምረት መሠረታዊ ግብዓት የሆነውን ፖታሽ ለማውጣት ፈቃድ ወስደው ያለ ሥራ ለረዥም ጊዜ የተቀመጡ ኩባንያዎች በዚህ ዓመት (2017) ሥራ ካልጀመሩ፣ ሕጋዊ ዕርምጃ እንደሚወሰድባቸው መንግሥት አስጠነቀቀ፡፡

በአፋር ክልል የፖታሽ ማዕድን ለማምረት ፈቃድ ለወሰዱ ኩባንያዎች፣ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ መጻፉን የማዕድን ሚኒስቴር በሪፖርቱ ጠቅሷል፡፡

ከእነዚህ ማስጠንቀቂያ ከተሰጣቸው ትልልቅ የፖታሽ አልሚ ባለፈቃዶች ውስጥ ሰርከም ሚኒራልስ፣ ያራ ዳሎልና ኢትዮ ፖታሽ የሚባሉ ይገኙበታል፡፡ ኩባንያዎቹ ፈቃድ ከወሰዱ ሰባት ዓመታት እንደሆናቸው ተገልጿል፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/133401/

**3. ሁሉም ንግድ ባንኮች በሒሳብ ዓመቱ ያስመዘገቡት ሀብት ከሦስት ትሪሊዮን ብር በላይ ተሻገረ**

**September 11, 2024**

የኢትዮጵያ የፋይናንስ ዘርፉ በተጠናቀቀው የሒሳብ ዓመት በሁሉም መመዘኛዎች ጤናማ ሆኖ ስለመቀጠሉ እየተገለጸ ነው፡፡ ከጥቂት ወራት በፊት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በመጀመርያው የፋይናንስ ዘርፍ መረጋጋት ሪፖርት ይፋ ባደረገበት ወቅት ይህንኑ አመላክቷል፡፡ በዚሁ ሪፖርቱ በኢትዮጵያ የፋይናንስ ዘርፍ ውስጥ ሥር የሰደደ ሥጋት ባይኖርም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አንዳንድ ሥጋቶች እየጨመሩ መምጣታቸውንና የፋይናንስ ሥርዓቱ ጤናማነትና ደኅንነት የበለጠ ለማረጋገጥ ተገቢውን ትኩረት መስጠትና የመከታተያ ዕርምጃዎች መውሰድ እንደሚገባ ማመላከቱ አይዘነጋም፡፡

እንዲህ ያለ ትንተና የተሰጠበት ይዘት በ2016 የሒሳብ ዓመት በተለይ የባንኩ ዘርፍ አጠቃላይ አፈጻጸም ሲታይ አሁንም በእሴት፣ በካፒታል፣ በትርፍና በተቀማጭ ገንዘብ አሰባሰብ በብድር ምጣኔው ዕድገት መቀጠል ስለመሆኑ የሒሳብ ዓመቱ ጥቅል አፈጻጸም የሚያሳይ ግርድፍ የሒሳብ ሪፖርት አመላክቷል፡፡ ከዚህ የሒሳብ ሪፖርት መረዳት እንደሚቻለው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ባንኮች በአትራፊነታቸው ቀጥለዋል፡፡ የባንኮች አጠቃላይ የሀብት መጠንም ከሦስት ትሪሊዮን ብር በላይ ስለመሻገሩ ያመላክታል፡፡

**https://www.ethiopianreporter.com/133345/**

**4.የዘረመል ቴክኖሎጂ መስፋፋት ለሆርቲካልቸር ዘርፍ ልማት ሥጋት መሆኑ ተገለጸ**

***September 15, 2024***

የዘረመል ቴክኖሎጂ መስፋፋቱና በጤና ላይ የሚያደርሰው አደጋ መበራከቱ፣ ለሆርቲካልቸር ዘርፍ ልማት ሥጋት መሆኑን፣ የግብርና ሚኒስቴር ያዘጋጀው የሆርቲካልቸር ልማት ግብይት ስትራቴጂ አመላከተ፡፡

ስትራቴጂው የተዘጋጀው ከ2016 እስከ 2025 ዓ.ም. ለመተግበር ሲሆን፣ የሆርቲካልቸር ዘርፍ እንዳያድግ ሥጋት ይሆናሉ ተብለው ከተዘረዘሩት መካከል የዘረመል ቴክኖሎጂ መስፋፋት መሆኑ ተገልጿል፡፡

ከዓለም አቀፉ የኃይል መቃወስ ጋር ተያይዞ የዘረመል ምርምርና ማምረቻዎች ወጪ እየናረ መምጣት፣ በዘርፉ የሚገኙ ተዋንያንን እየተፈታተነ መሆኑ በስትራቴጂው ተመላክቷል፡፡

**https://www.ethiopianreporter.com/133372/**

**5. የኢትዮጵያ የቱሪዝም ሳተላይት አካውንት ነገ ይፋ ይደረጋል - የቱሪዝም ሚኒስቴር**

**ኢ.ዜ. አ መስከረም 6/2016**

ማስረጃን መሰረት ያደረገ ፖሊሲ መቅረፅና ውሳኔ መስጠት የሚያስችል የቱሪዝም ሳተላይት አካውንት ነገ ይፋ እንደሚደረግ የቱሪዝም ሚኒስቴር ገለጸ፡፡

በዓሉ ከምስራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግስታት ባለስልጣን (ኢጋድ) እና ከተባበሩት መንግስታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ጋር በመተባበር ከነገ ጀምሮ ለሶስት ቀናት ይከበራል ብለዋል።

**https://www.ena.et/web/amh/w/amh_5156456**

**5.ኢትዮጵያ ወደ ቻይና የምትልካቸውን ምርቶች በብዛትና በአይነት ለማስፋት እየሰራች ነው - አምባሳደር ተፈራ ደርበው**

**ኢ.ዜ.አ መስከረም 6/2017**

ኢትዮጵያ ወደ ቻይና የምትልካቸውን ምርቶች በብዛትና በአይነት ለማስፋት እየሰራች እንደምትገኝ በቻይና የኢትዮጵያ አምባሳደር ተፈራ ደርበው ገለጹ።

ዓለም አቀፍ የንግድ አገልግሎት ሁነት በቤጂንግ ተካሄዷል።

በቻይና የኢትዮጵያ አምባሳደር ተፈራ ደርበው የንግድ ሁነቱን፣ የኢትዮጵያና ቻይና የሁለትዮሽ ግንኙነትን አስመልክቶ ከቻይና ግሎባል ቴሌቪዥን ኔትወርክ (ሲጂቲኤን) ጋር ቆይታ አድርገዋል።

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_5155107

**6.የኢትዮጵያ የዘወትር መሻት ፍትሃዊና ምክንያታዊ በሆነ አግባብ የውሃ ሃብቷን ተጠቅማ ልማቷን ማረጋገጥ ነው**

**ኢ.ዜ. አ መስከረም 5/2017**

የኢትዮጵያ የዘወትር መሻት ፍትሃዊና ምክንያታዊ በሆነ አግባብ የውሃ ሃብቷን ተጠቅማ ልማቷን ማረጋገጥ ነው ሲሉ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አምባሳደር ታዬ አጽቀሥላሴ ተናገሩ፡፡

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አምባሳደር ታዬ፤ ኢትዮጵያ ያሏትን የተፈጥሮ ሃብቶች ተጠቅማ ልማቷን ለማረጋገጥ በትኩረት እየሰራች መሆኑን ነው ለኢዜአ የተናገሩት።

**https://www.ena.et/web/amh/w/amh_5153244**

**7.የቅዳሜና እሁድ ገበያዎች ፍትሃዊ የግብይት ሰርዓት እንዲኖር ከፍተኛ ሚና እያበረከቱ ነው - ካሳሁን ጎፌ (ዶ/ር)**

**ኢ.ዜ.አ ፡መስከረም 5/2017**

የቅዳሜና እሁድ ገበያዎች ፍትሃዊ የግብይት ሰርዓት እንዲኖር ከፍተኛ ሚና እያበረከቱ መሆኑን የንግድና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስትር ካሳሁን ጎፌ(ዶ/ር) ገለጹ

መንግስት ምክንያታዊ ያልሆነ የአቅርቦት እጥረትና የዋጋ ንረት እንዲከሰት የሚያደርጉ ነጋዴዎች ህጋዊ መስመር እንዲይዙ የተለያዩ እርምጃዎችን ሲወስድ መቆየቱን አንስተዋል፡፡

በህገወጥ ነጋዴዎች ላይ ከሚወሰደው እርምጃ ጎን ለጎን የቅዳሜና እሁድ ገበያዎች እንዲጠናከሩ የተለያዩ ስራዎች እየተከናወኑ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

መንግስት ምክንያታዊ ያልሆነ የአቅርቦት እጥረትና የዋጋ ንረት እንዲከሰት የሚያደርጉ ነጋዴዎች ህጋዊ መስመር እንዲይዙ የተለያዩ እርምጃዎችን ሲወስድ መቆየቱን አንስተዋል፡፡

በህገወጥ ነጋዴዎች ላይ ከሚወሰደው እርምጃ ጎን ለጎን የቅዳሜና እሁድ ገበያዎች እንዲጠናከሩ የተለያዩ ስራዎች እየተከናወኑ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ይህ ተግባር በቀጣይም ተጠናክሮና እንደሚቀጥል ገልጸው፤ ባለድርሻ አካላትም የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_5153108

### 8.የአምራች ዘርፉን እድገት የሚያፋጥኑት የኢንዱስትሪ ፓርኮች

**September 12, 2024**

የኢንዱስትሪ ፓርኮች (Industrial Parks) ልማት የኢትዮጵያን መዋቅራዊ የምጣኔ ሀብት ሽግግርን እውን ለማድረግ አስተዋፅዖ ይኖራቸዋል ተብለው ትኩረት ከተሰጣቸው ተግባራት መካከል አንዱ ነው። የኢንዱስትሪ ፓርኮች የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት የመሳብ፣ የሥራ እድል ፈጠራን የማስፋት እና የቴክኖሎጂ ሽግግርን እውን የማድረግ ዋና ዋና መሰረታዊ ተልዕኮዎች አሏቸው። ፓርኮቹ በሚገነቡባቸው አካባቢዎች ለሚኖረው የኅብረተሰብ ክፍል ስራ በመፍጠርና ከአካባቢ ጋር ተስማሚ የሆነ የሥራ ከባቢ እውን በማድረግ ለሀገራዊ የምጣኔ ሀብት እድገት ትልቅ አስተዋፅዖ ይኖራቸዋል።

በአሁኑ ወቅት የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጣናን ጨምሮ በመላ ሀገሪቱ 13 የኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚገኙ ሲሆን በስራ እድል ፈጠራ፣ በውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትና በቴክኖሎጂ ሽግግር ለሀገራዊ ምጣኔ ሀብት እድገት አስተዋፅዖ እያበረከቱ ይገኛሉ።

የእነዚህ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት የኢንዱስትሪውን ዘርፍ ለማሳደግ ከተደረጉት ጥረቶች መካከል የሚጠቀስ ሲሆን፣ በመንግሥት እየተወሰዱ ያሉትን የኢኮኖሚ ማሻሻያ መርሃ ግብሮችን ከግምት ውስጥ ባስገባ መልኩ ፓርኮቹም ዘርፉን የማሳደግ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

https://press.et/?p=136481

## በውጭ ቋንቋዎችና ከውጭ ሚዲያዎች

### 9.Ministry pins horticulture export dreams on ambitious strategy

**Reporter: September 14, 2024**

Ethiopia's lucrative horticulture trade could stumble as exporters transfer rising production and research and development costs to their products, potentially discouraging international buyers, warn experts at the Ministry of Agriculture.

The cost of horticulture research and production arising from the global energy crisis is making horticulture products expensive. Exporters are transferring these additional prices to end consumers. As a result, international horticulture consumers are being discouraged," reads the Ministry's horticulture development and marketing strategy.

https://www.thereporterethiopia.com/41879/

### 10.Palace admin. to engage in hospitality, real estate businesses

**Reporter: September 14, 2024**

The Council of Ministers has approved new legislation that would enable the administration of palaces across the country to lease out space for various hospitality and commercial services.

Approved a month ago, the regulation grants the Palace Administration the right to lease out property for use by resorts, spas, equestrian ranches, and other businesses.

https://www.thereporterethiopia.com/41876/

### 11.Safaricom on track for full coverage in eastern Ethiopia by October

**Reporter; September 14, 2024**

Executives at Safaricom Telecommunications Ethiopia say the company will begin offering full coverage of eastern Ethiopia by the end of next month, marking a significant milestone two years after launch and nearly three-and-a-half years into its 15-year license.

**https://www.thereporterethiopia.com/41873/**

### 11.Ethiopian Airlines Wins Prestigious 'Outstanding Tourism Transportation Award'

**ENA:September 13/2024**

The Ethiopian Airlines Group won the Prestigious 'Outstanding Tourism Transportation Award' at Africa Tourism Leadership Forum.

Ethiopian Airlines is thrilled to announce that it has been bestowed with the coveted 'Outstanding Tourism Transportation Award' at the 2024 Africa Tourism Leadership Forum (ATLF) held in Gaborone, Botswana," the group stated.

This prestigious accolade recognizes tourism transportation organizations that consistently deliver the highest standards of service to travelers while upholding strong sustainability and environmental credentials.

**https://www.ena.et/web/eng/w/eng_5147450**

### 12. Ethiopia's coffee export hits record high profit

**Ethiopian press: September 14, 2024**

Ethiopia has secured a record-breaking profits of over 196 million USD from 42,322 tons of exported coffee just last month, Ethiopian Coffee and Tea Authority announced.

The information obtained from the authority indicated that the country has generated over 196 million USD exporting 42,322 tons of coffee last month, a record high foreign currency earnings registered in a month from the export of the cash crop in the history of the country.

**https://press.et/herald/?p=102302**

### 13.Ethiopia to exploit full potential of solar energy to accelerate energy transition

**Ethiopian press: September 15, 2024**

Ethiopia is increasingly identifying the urgent need to transition from traditional energy sources to more sustainable alternatives. Among these, solar energy emerges as a beacon of hope, poised to transform Ethiopia's energy landscape and drive socioeconomic development. Significantly, the country has relied heavily on hydropower, which accounts for more than 90% of its electricity generation. While this reliance has positioned the country as one of Africa's leading producers of renewable energy, according to the studies.

### 14. Currency Devaluation and The Poor: An Empirical Analysis

**Capital: September 9, 2024**

Currency devaluation involves reducing the value of a country's currency relative to other currencies. While it can help boost exports and reduce trade deficits, its effects on different income groups, particularly the poor, are complex and multifaceted. This article investigates how devaluation impacts impoverished populations, focusing on the interplay between macroeconomic changes and individual economic conditions.

Currency devaluation lowers the exchange rate, making exports cheaper and imports more expensive. This can stimulate domestic production and reduce trade deficits. However, the theoretical benefits of devaluation come with potential downsides, particularly for low-income individuals who may face increased living costs without corresponding income growth.

https://www.capitalethiopia.com/2024/09/09/currency-devaluation-and-the-poor-an-empirical-analysis/